# የጉዞ ማስታወሻ

በጌታቸው አሸኔ

«ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም!» ይባላል።

ምሳሌነቱ፣ ሞኝ ሰው ባንድ ወቅት የሰማውን ነገር ደጋግሞ ስለሚናገር፣ ወረቀትም ላይ የሰፈረ ቃል ለብዙ ጊዜ ስለሚቆይ ነው። ቢሆንም ቅሉ፣ዛሬ ላይ ሆኜ ያለፈውን ታሪክ ከማስታወሻ ደብተሬ ላይ ሳነበው፣ መልካሙን የትዝታ ዘመን ስለሚያስታውሰኝና ውስጤ በደስታ ስለሚሞላ፣ ማስታወሻ ያሰፈርኩበት ወረቀት "ለምን በሞኝ ተመሰለ?" ብዬ እቆጫለሁ።

የማስታወሻን ጥቅም የምንገነዘበውና የምናደንቀው እጅግ ቆይተን ስናገኘው በመሆኑ!

ያለፈን ታሪክ ማንሳቴ ላለፉበት ሰዎች ትዝታን ለመጫር፣ ላልደረሱበት ደግሞ በመጠኑም ቢሆን ስለነበረ ሁኔታ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ብዬ ነው።

ወደ ርዕሴ ልመለስና በተለያዩ ጊዜያት ስለጎበኘሁት አንድ የጉዞ መዳረሻ ላውራችሁ፣ሩቅም አይደል ቅርቡ ኤርትራ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አስመራ የሄድኩት በነሐሴ ወር 1963 ዓ.ም ነበር፤ በወቅቱ <Carlo Erba> የተባለ የመድኃኒት አስመጪና አከፋፋይ ድርጅት ውስጥ እሠራ ስለነበር፣ ለኤርትራ ክልል አሥመራ ላይ ወኪላችን የነበረን ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ ኢንስፔክት/ኦዲት ለማድረግ ተልኬ ነበር። በነገራችን ላይ በዚያን ጊዜ አንድ አስመጪ ድርጅት consignment ውል፣ዕቃን ለሽያጭ ወኪሉ እየላከ ፣ ወኪሉ ደግሞ ከሸጠው ጠቅላላ ዋጋ ላይ የሚደርሰውን ኮሚሽን ቀንሶ የሚከፍልበት የተለመደ የንግድ አሠራር እንደነበር ማስታወስ እሻለሁ። ከዚህ ድርጅትም ጋር የነበረን የንግድ ውል በዚህ አሠራር ላይ የተመሠረተ ነበር።

አስመራ በሥርዓት የተቀየሰ ውብ ከተማ ሲሆን፣ያረፍኩበትም ሆቴል መሃል ከተማ በወቅቱ «ጎዳና እቴጌ መነን» ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነበር። የመንገዱ ስፋትና በመሃሉ የተተከለው የዘንባባ ዛፍ ለከተማው ልዩ ውበትን አጎናጽፎታል። ከሥራ ሰዓት በኋላ ወደማታ አየሩ ነፋሻማ ስለሚሆን፣በጎዳናው ግራና ቀኝ አዘውትሮ ሽርሽር የመውጣት ልምድ በብዛት ይታያል። ካፌና ሬስቶራንቱም የፀዳና አመሻሹ ላይ በኤሌትሪክ ብርሃን ደምቆ ለመስተንግዶ ተዘጋጅቶ ስለሚጠባበቅ፣ጎራ ብሎ መዝናናቱ የተለመደ ባህል ነበር። በወቅቱ የአብዛኛዎቹ ሬስቶራንቶችና ሆቴሎች ባለቤቶች የኢጣሊያን ተወላጆች ስለነበሩ፣የምግብ ዓይነቱ (menu) ሆነ መስተንግዶው ግሩምና የተሟላ ነበር። የአስመራ ኤክስፖ (Asmara Expo) ታላቅ ባዛርና የንግድ ትርዒትም በዚያው ዓመት የተስተናገደበት ወቅት ስለነበር፣ ከተማው አሸብርቆና ደምቆ ይታይ ነበር። የሕዝቡም ቀናነትና እንግዳ ተቀባይነት ይመስጥ ነበር፣ በተለይም ከመሃል አገር ለመጡ እንግዶች የተለየ ፍቅር ያሳዩ ስለነበር አስመራን ለመጎብኘት እድል በማግኘቴ ደስተኛ ነበርኩ።

በያኔዋ አስመራ የታወቀው የምሽት ክለብ «ሞካምቦ» ይባላል፤ የአዳራሹ ስፋትና የጣሪያው ከፍታ ከአድማቂ መብራቶቹ ጋር የሚቸጎደጎደው ሙዚቃና መድረኩን የሞላውን ተውረግራጊ ዳር ቆሞ ለተመለከተው ልዩ ትርዒት ነበር። ከአገር ውስጥ በተጨማሪ፣ የእንግሊዝኛና የሱዳን ሙዚቃዎች ይዘፈናሉ። በዚያን ጊዜ «ቃኘው ሠፈር» (Kagnew Station) የተባለ በአስመራ የሠፈሩ የአሜሪካን ወታደሮች የሚኖሩበት ክልል ነበርና እነዚህ ወታደሮች ቅዳሜ ማታ በብዛት ወደ ሞካምቦ ክለብ ይመጣሉ፤ ከነዚህም መካከል የሙዚቃ ተሰጥኦ ያላቸው በፈቃደኝነት መድረክ ላይ ወጥተው በመዝፈን ታዳሚውን ሞቅ ባለ የሮክ ኤንድ ሮል ሙዚቃና ዳንስ ያዝናኑት ነበር። በእኔ ግምት በወቅቱ በየትኛውም የአገሪቱ ከተሞች እንደ ሞካምቦ ያለ የደመቀ የምሽት ክለብ ያለ አይመስለኝም። ሁሉም ሰው ከመደሰት በስተቀር ረብሻ ወይም ጥል አላየሁም፣ ያሻው ሲደንስ ያነጋል የደከመው ደግሞ ተኮልኩለው ከሚጠባበቁት የማሾ መብራት ከተገጠመላቸው የፈረስ ጋሪዎች በአንዱ ተሳፍሮ ይሄዳል፤ የሰዓት እላፊ የለ፣ቀማኛና ማጅራት መቺ አያስፈራ። ግሩም የደስታ ጊዜ ነበር!

የአስመራ ቆይታዬን እንድወደው ካደረጉት አንዱ አቶ ተስፋዬ ወ/ማርያም ነበር፣ (እግዚአብሔር ነፍሱን ይማር!)፤ተስፋዬ ከኮሜርስ የ1949 ዓ.ም ምሩቃና የማህበራችን አባል፣በወቅቱ በአስመራ የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ኃላፊ ነበር። ተስፋዬ በአለባበሱ ሽክ ያለ፣ ዘናጭና ተጫዋች ነበር። የቅርጫት ኳስ ጨዋታ ላይ በሚያሳየው ቅልጥፍጥፍ ያለ የአጨዋወት ዘዴ የተነሳ የቅርብ ጓደኞቹ ባወጡለት «ተስፋዬ ላስቲክ» በሚል የቅጽል ስም ይታወቃል። ወደ ማታ ካረፍኩበት ሆቴል መጥቶ ይወስደኝና የተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎች

እንሄድ ነበር። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ሴቶች በጐ አድራጎት ይሁን/የመኮንኖች ባለቤቶች ለማህበራቸው የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት( Fund Raising Dinner Party) አዘጋጅተው ነበርና በርሱ አማካኝነት የመግቢያ ቲኬት አግኝቼ ልሳተፍ ችያለሁ። የማይረሳኝ ክስተት፣ በፕሮግራሙ መደምደሚያ «የምሽቱ ንግሥት (Queen of the Night)» ምርጫ ይካሄድ ነበር፣አሸናፊዋ ንግሥትም የምትመረጠው በዳንስ መድረኩ ብዙ ቲኬቶች የተበረከተላት በመሆኑ፣ ብዙዎች ወንዶች ቲኬት በመግዛት ከሚመርጧት ሴት ጋር አዘውትረው ይደንሱ ነበር፤በመሃሉ ደግሞ ሌላው አድናቂ ጣልቃ በመግባት የዳንስ ትኬት አበርክቶ በመንጠቅ ያስደንሳት ነበር። በእንደዚህ ያለ ፉክክር ላይ አንዱ ቲኬት ሰጥቶ ዳንሱን ሳያበቃ፣ሌላው ተተክቶ ሲወስዳት ውድድሩ ይዘልቃል። በዚህ ሂደት ታዲያ ውድድር እንጂ ጥልና አምባጓሮ አይታይም። በመጨረሻም አንድ ፎልፏላ ልጃገረድ የብዙ ቲኬቶች አሸናፊ ተብላ ተሰየመች፤ታዳሚውም ሁሉ አጨበጨበላት። ኋላ ላይ ስለ ልጅቷ ማንነት ስጠይቅ የክ/ሀገሩ ፖሊስ ዋና አዛዥ የነበሩት ልጅ መሆንዋ ተነገረኝ። የኛም ቲኬት አስተዋጽኦ ስለነበረበት በአሸናፊዋ ልጅ ደስ ብሎን ወደ ወንበራችን ስንመለስ፣ ለካ አብረውን የመጡትን ሴቶች ሳናስደንስ ረስተናቸው ኖሮ አኩርፈው ጠበቁን፤ ስለዚህም ተኮራርፈን ተለያየን።

በማግስቱ ጠዋት ወደ ምፅዋ ለመሄድ ከወዳጄ ከበየነ ገ/ሕይወት ጋር ተቀጣጥረን ነበር፤ በየነ የኸክስት ኢትዮጵያ (Hoechst Eth.) የመድኃኒት አስመጪ ድርጅት የአስመራ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ነበር። በቮልስ መኪናው ጊንድዓን፣ ሴዲችን(16)፣ ነፋሲቲን ወዘተ አልፈን ቁላማውንና ቁልቁለቱን መንገድ ተወጣነው።ምፅዋ ከመድረሳችን በግምት ከ30-40 ኪ/ሜትር ላይ በስተግራ ዶጋሊ ይታያል፣ በስተቀኝ በኩል (እንደነገሩኝ) በጣሊያኖች ቦን እስፒሮ (bon spiro) ተብላ የተሰየመች ነፋሻማ የሆነች በተለይ የጣልያን ዜጎችና ከበርቴዎች የመኖሪያ መንደር ትገኛለች።

ምፅዋ ከምሳ ሰዓት በፊት ደርሰን፤ሻንጣችንን ያረፍንበት ቤት አስቀምጠንና የዋና ልብስ ለብሰን ወደ ባሕሩ ዳርቻ/ ጉርጉሱም አመራን። የባሕሩ ጥራት ኩልል ያለ ውሃ-ሰማያዊ ነው፣የአሸዋውም ንፃት እንደ መስታወት ያንፀባርቃል። ጊዜ ሳናጠፋ ወደ ባሕሩ ገባን፤ መለስተኛው ማዕበል ሳያሸንፈን ወደ መሃል ዘለቅን። ዕለቱ እሁድ ስለነበር ዋናተኛው ብዙ ነበር፤ወንዱ ሴቱ፤ ጎልማሳው፤ ሽማግሌና አሮጊቱ ሳይቀሩ ባሕሩ ውስጥ ይንቦጫረቃሉ። ከብዙ ሰዎች መሃል አንድ ሰው ስሜን ሲጣራ ዞር ብዬ ሳየው የወኪላችን ድርጅት ተላላኪ መሆኑን ተረዳሁና፣ እንዴት እንደመጣ ጠየኩት። በኔ ግምት እዚህ የመዝናኛ ቦታ ለመገኘት ለአንድ ተላላኪ ይከብደዋል ብየ በማሰብ ነበር። የሰጠኝ መልስ ግን ከሚያገኛት አነስተኛ ደመወዝ በመቆጠብ በየእሁዱ በአውቶብስ ተሳፍሮ እንደሚመጣና ሲዋኝ ቆይቶ ማታውኑ እንደሚመለስ ነበር። በዚያን ጊዜ አነስተኛ ደሞዝተኛ ቀርቶ ደህናም ገቢ የነበረው የመሃል አገር ሰው ይህን መሰል የመዝናኛ ባህል አልነበረውም ነበር።

ዋናው አብቅቶ ለመታጠብ ሻወር ስንገባ ከበንቧው የሚወርደው ውሃ በፀሐዩ ንዳድ የጋለ በመሆኑ ገላን ያቃጥል /ይልጥ ነበር። የውሃ ጥሙም ጊዜ የማይሰጥ ስለነበር ሮጠን ትልቁን ባለ 650 ሲ/ሲ መሎቲ ቢራ ተያያዝነው። በወቅቱ የመሎቲ ቢራ አ/አበባም ላይ እጅግ ተወዳጅ ቢራ ስለነበር ሁሉም በያለበት ትልቁን ጠርሙስ ቢራ ተያይዞ ይጎነጨዋል፣ላብ እንደውሃ ይፈሳል እንጂ ሞቅታ አልነበረም። ከሬስቶራንቱ የቀረበልንም የጣሊያን ምግብ የመጣፈጡ ብዛት እንኳን የራበው የጠገበም አይምረው።

ምፅዋ ማታም ላይ ደማቅ የወደብ ከተማ ነበረች፤የአብዛኛዎቹ ቤት አሠራር ዋናው መኖሪያ ከፊት ለፊት ሆኖ፣የሰርቪስ ክፍሎቹና ግቢው በስተጀርባ የተከለለ ነው። ከቤቱ ጣሪያ ላይ በጀርባ በኩል የመወጣጫ ደረጃ ያለው ቀን-ቀን ወጥቶ ለመዝናናት፣ በሙቀቱ ወራት ደግሞ የመኝታ አልጋና ፍራሽ ተነጥፎ የተዘጋጀበት ልቅ ወለል (floor) ይገኛል። ይህም የቤት አሠራር የአረብ ተጽእኖ ያለበት ይመስላል፣ ምክንያቱም ቀደምት ከከተሙት ነዋሪዎች የየመን ተወላጆች እንደሆኑ ስለሚነገር ነው። ሁለታችንም አልጋ ተዘጋጅቶልን የተኛነው እዚህ ልቅ ቦታ ነበር። ከብዙ ርቀት ላይ ከሚታዩት ከዋክብት በስተቀር ሰማዩ የጠራ ነበር። የቀኑ ድካምና የቢራው መጠን ተዳምሮ በጊዜ ለሽ አልኩ። ሊነጋጋ ሲል ከእንቅልፌ ስነቃ ወደላይ የተመለከትኩት ጣሪያ ሳይሆን የሰማዩን ከዋክብትና ልትጠልቅ የተቃረበች ጨረቃን ነበር፣ ዙሪያውንም ሳማትር የታየኝ የተዘረጋው ባሕር ነው። የተኛሁበትን ቦታ ፈጽሜ ረስቼው ስለነበር «የት ነው ያለሁት»? ብዬ ላጭር ጊዜ በድንጋጤ ክው ብዬ ቀረሁ።

በነጋታው ከተማውን እየተዘዋወርን ስንመለከት በዘመናዊ አሠራር (luxury) ከሚደነቁት ቤቶች አንዱ የሆነውን የሲኞራ መሎቲ የዕረፍት (week end) ማረፊያ ቤት አሳዩኝ፣ ይህ የመኖሪያ ቤት ከላይ የተራራውን መልካ ምድር ተንተርሶ እስከ

ባህሩ የሚዘልቅ ሰፊ ቦታን ያካተተ ውብና ምርጥ ቤት ነበር። እንዲህ የተንደላቀቀ ቤትና ኑሮ ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት ምፅዋ እንደነበር ትገምቱ ይሆን? ያለፈን ታሪክ አንስቶ "ድሮ ቀረ" ማለቱ ልማዳዊ አባባል ቢመስልም፣የአስመራና ምፅዋ ውበትና ድምቀት ግን ያልተጋነነ እውነታ ስለነበር አድናቆቴ ተገቢ ነው። የአስመራና ምፅዋ ጉብኝቴን በዚሁ አስደሳች ቆይታ አጠናቅቄ ቻው ቤላ! ብዬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አስመራ የበረርኩት ከዛሬ 26 ዓመት በፊት በመስከረም 1981 ዓ/ም መሆኑን በወቅቱ አጀንዳዬ ላይ ጽፌ ያሰፈርኩት ማስታወሻ (diary) ያመለክታል። በዚያን ጊዜ የተሠማራሁበት ሥራ በመላው ዓለም ታዋቂ የሆነው የኤስ.ጂ.ኤስ. ኢንስፔክሽን ኩባንያ /በኢትዮጵያ የንግድ ተጠሪ (commercial rep.) ሆኜ ነው። ኤስ.ጂ.ኤስ ኩባንያ፣ የአውሮፖ ልማት ማህበር የሚለግሰውን የምግብ እርዳታ በተመለከተ፣ የጥራትና የመጠን ኢንስፔክሽን አገልግሎት (Quality and Quantity Inspection /verification) እንዲያከናውን የተሰየመ ነበር፤ ስለዚህም በአሰብና በምፅዋ ወደቦች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የምግብ/እህል እርዳታን አስመልክቶ ጥራትን በተመለከተ፣ ወደብ ላይ አማካኝ ናሙና (representative sample) እንዲወስድ በማድረግ መጣኝ ናሙናውን በሚገባ ታሽጎ ፈረንሣይ ፓሪ ለሚገኘው ላብራቶሪ (S.G.S. Qualities, Laboratory Crepin) ይላክ ነበር። መጠንን /ብዛትን በተመለከተ ደግሞ ወደብ ላይ በ3 ፈረቃ/24 ሰዓት ሙያተኞችን በመመደብና ከወደብ ገቢ ሰነዶች ጋር በማመሳከር ብዛቱን የሚገልጽ መረጃ ጄኔቭ/ሲዊዘርላንድ ለሚገኘው የኤስ.ጂ.ኤስ ኢንስፔክሽን ኩባንያ ዋና መሥሪያ ቤት አስተላልፍ ነበር። አብዛኛው ሥራዬ ግን አሰብ ወደብ ላይ ስለነበር አዘውትሬ የምሄደው ወደ አሰብ ነበር።

መቼም አሰብ ከተነሳ ለከተማውና ለወደቡ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ባለውለታዎቹ አንዱ የነበሩትን ኮማንደር ዘለቀ ቦጋለ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል። እኚህ የባሕር ኃይል ኮማንደር የኢት.ወደቦች አገልግሎት ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ የአሰብ ወደብን በማስፋፋትና የሠራተኞችን እንክብካቤ ከማሻሻል አልፈው፣ የከተማውን ውበት በዛፍ ተከላ እና ደረጃውን የጠበቀና ያማረ የእንግዳ ማረፊያ ቪላዎች በባሕሩ ዳርቻ እንዲገነቡ በማድረግ ገጽታው እጅግ እንዲለወጥ አድርገዋል።

ወደ ሌላው ወቅት የሥራ ጉዞዬ ልመለስና፣እ.ኤ.አ September 1988 ከኢጣሊያን ኤምባሲ ይደወሉና፣ምፅዋ ወደብ ላይ በኮንቴይነር ታሽጎ የተጫነ የእርዳታ ምግብ በቅርብ ቀን ስለሚደርስ ብዛቱንና ጥራቱን በተመለከተ በአስቸኳይ ኢንስፔክት እንድናደርግ ይጠይቁናል። በዚያን ወቅት በሰሜኑ ኢትዮጵያ የአስቸኳይ ጊዜ የታወጀበት አልፎ አልፎም ጦርነት ያልበረደበት ክልል በመሆኑ ብድግ ተብሎ የሚኬድበት አልነበረም። ሆኖም የሥራ ትዕዛዝ ሲመጣ ምክንያት መደርደር ስላልፈለግሁ ፈቃደኝነቴን ገልጬና ዋናው መ/ቤቴን አሳውቄ፣የእርዳታ ምግቡን በተመለከተ መጫኛ ሰነድ (Bill of lading) እና ዝርዝር መረጃዎችን ከአ/አበባ ቆንስላው ጽ/ቤት ተቀበልኩ።በሌላ በኩል ከሣምንት በፊት ባለቤቴ (ከሁለት ተከታታይ ወንድ ልጆች በኋላ) ቀጣይዋን ሴት ልጃችንን የወለደች በመሆኑ የሴተሰቡን የደስታ ስሜት ላለመበረዝና ሃሳብ ውስጥ ላለመጣል ብዬ፣ አዘውትሬ ወደምበርበት አሰብ ለሥራ የምሄድ መሆኑን ለባለቤቴ ነገርኳት።

የተላከው የእርዳታ ምግብ የታሸገ ብስኩት ሲሆን፣ይህም «አንድነት» (ANDINET) በተባለው የኢትዮጵያ መርከብ መጫኑን ከተያያዘው ሰነድ አረጋገጥኩ፤ የኢት.መርከብ ድርጅት (E.S.L) በሚያስተላልፈው መረጃ (E.S.L.-Shipping Bulletin) መሠረት መርከቡ ምፅዋ ወደብ የሚደርሰው እ.ኤ.አ October 06/1988 መሆኑንም ተረዳሁ።

በዚህ መሠረት የጉዞዬን እቅድ (booking) በኢት.አየር መንገድ - በ04/10 - ADD/ASM/ በ05/10- ASM/MASS እና ከዚያም መልስ በ07/10 MASS/ASM በ08/10- ASM/ADD ተመዝግቤ የጉዞ ቲኬት አስቆረጥኩ።

ማክሰኞ እ.ኤ.አ October 04,1988 ከአዲስ አበባ በመብረር አስመራ ተሰዓት በኋላ በ10:30 ደረስን፣ በ11:00 ሰዓት እምባሶራ ሆቴል ገባሁ። መምጣቴንም አስመራ ለሚገኘው የኢጣሊያን ቆንስላ ጽ/ቤት በመደወል አሳውቄ፣ ወደምፅዋ አብሮኝ የሚበረውን ባልደረባ እንዲያሳውቁኝ ጠየቅኋቸው። በቆንስላው የተመደበውና አብሮኝ የሚጓዘው የሎጂስቲክስ አስተባባሪ የነበረው (Signor Lucio Di Mascio) ያረፍኩበት ሆቴል ድረስ ማታውኑ እንደሚመጣና ስለጉዞው ሁኔታ እንደሚያነጋግረኝ ገለጹልኝ። በወቅቱ አስመራ የሰዓት እላፊ የታወጀበት ከተማ በመሆኑ፣ሁሉም ነዋሪ (ከፀጥታ አስከባሪዎች በስተቀር) ከምሽቱ በ1:00 ሰዓት በየቤታቸውና ባረፉበት ሆቴል አስቀድሞ ይገኛሉ እንጂ፣ያለ ፈቃድ የሚዘዋወር ሰው አይታይም ነበር። አጋጣሚ ሆኖ እዚሁ ሆቴል ከኔ ቀደም ብለው ጓደኛዬ ተሠራ-ወርቅ

ሽመልስ (በወቅቱ የሕጻናት ኮሚሽን ተ/ኮሚሽነር) እና የተከበሩ አቶ መኮንን ዘውዴ (የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት መሥራችና የቦርድ ሰብሳቢ) አርፈው ነበር። የመጡበትም ምክንያት አስመራ ላይ በድርጅቱ እርዳታ የተቋቋመውን ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት ማሳደጊያ ለማስመረቅ ነበር። አንድም የማከብራቸውን አቶ መኮንን ዘውዴ (በነገራችን ላይ ባለቤታቸው ወ/ሮ ያይን አበባ ሸዋንግዛው የት/ቤታችን/ኮሜርስ ላይብሬሪያን ነበሩ፤) እንዲሁም የቅርብ ጓደኛዬ ተሠራወርቅ ሽመልስን በማግኘቴና በማውቃቸው ወዳጆች መካከል በመገኘቴ ተረጋግቼ ደስ ብሎኝ ነበር። የሁለቱንም ነፍስ ይማር!

አመሻሹ ላይ እዚያው ሆቴላችን እራት እየበላን ሳለ፣የከባድ መሣሪያ ተኩስ ይሰማ ጀመር፤ሁላችንም ላይ የፍርሃት ድባብ ይታይ ስለነበር በጊዜ ከመተኛት ይልቅ እዚያው ቡና ቤቱ አዳራሽ መቆየቱን መረጥን። ከሆቴሉ የነበርነው እንግዶችም በጣም ጥቂቶች ነበርን። ከቡና ቤቱ እየተጫዋወትን ሳለን፣በጊዜ ይመጣል የተባለው Signor Di Mascio ከምሽቱ 4:00 ገደማ ከሌሎች እንግዶች (አንደኛው በቅርብ የምናውቃቸው) ጋር በመሆን እንደ ድንገት ገብተው ተቀላቀሉን። በሁኔታው በመገረም በዚህ የከባድ መሣሪያ ተኩስ በሚሰማበት ወቅት እንዴት ደፍረው እንደመጡ ስንጠይቃቸው የሰጡን መልስ፣ ስጋት የሚገባቸው የተኩስ ድምጽ ሲጠፋ እንጂ፣ የየምሽቱን ተኩስ የለመዱት መሆኑን በመግለጽ ነበር። በሌላም በኩል የዲፕሎማቲክ ሰሌዳ በለጠፈ መኪና ስለሚጓዙ የሰዓት እላፊው የማይመለከታቸው መሆኑን ተረዳን።

Signor Di Mascio የመጣው በማግስቱ አብረን ወደ ምፅዋ ስለምሄድበት ሁኔታ ለመነጋገር ስለነበረና እኔም ከአስመራ ወደ ምፅዋ ለመብረር የደርሶ መልስ ጉዞ ትኬት ያስቆረጥኩ መሆኑን ገልጬለት፣ የምንበርበትን ሰዓትና ተያያዥ ጉዳዮችን ጠየቅሁት። ሆኖም ከአስመራ ወደ ምፅዋ የነበረው በረራ ለደህንነት ሲባል ቀድሞውኑ የተቋረጠ መሆኑን አስረድቶኝ፣ ጉዟችን በመኪና መሆኑን አረዳኝ። በዜናው መደንገጤን ተገንዝቦ የምንጓዝበት መኪና የእርዳታ ድርጅት ሠሌዳ ያለው በመሆኑ ምንም ዓይነት ስጋት እንዳያድርብኝ አረጋግቶና አሳምኖ ገለፀልኝ።

በዚሁ ተስማምተን የመነሻ ሰዓት ከወሰንን በኋላ፣በል ደህና እደር ብዬ ስሰናበተው እርሱ ግን ይቀጥልና የአስመራ ምሽት ክለቦችን (በእርሱ አነጋገር «secreto») ላስጎብኝህ በማለት ይጋብዘኛል። በዚያ ምሽት እንኳን ደፍሬ ልወጣ፣ ሆቴልም ውስጥ ስጋት ላይ ያለሁትን ባይተዋር ሰው ወደ ምሽት ክለብ እንሂድ ሲለኝ፣ይህ ሰው ጤነኛ አይደለም ብዬ ተጠራጠርኩት። ግና እኔ ሳገሩ ባዳ ሆኜ ተጠራጠርኩ እንጂ፣አብረውት የነበሩና የሚያመሻሹት አበሾችም ነበሩ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ከተማና ከቅርብ ርቀት የተኩስ ድምጽ በሚሰማበት ሠፈር የ«አስረሽምቺው» ምሽት ክለብ መኖሩና ሰውም ደፍሮ መዝናናቱ በጣም ገረመኝ። ባልደረባዬ Signor Di Mascio ምንም ክፋት የሌለው፣ መልካምና ደስታን ፈላጊ መሆኑን በኋላ ላይ አብረን ባሳለፍናቸው ጊዜያት ተረዳሁ።

በማግስቱ 4 ሰዓት ላይ ከአስመራ በመነሳት ጊንዳዓ መውጫ በር (check point) አልፈን ቁልቁለቱን የምፅዋ በረሃማና ጠመዝማዛ መንገድ ተያያዝነው። አስመራ ወይና ደጋ የሚባል የአየር ንብረት ያለው ሲሆን ቁልቁለቱ ወደ ምፅዋ የሚወስደው ግን በረሃማና ሞቃታማ ነው፤ በመንገዱ ላይ ብዙም የሚጓጓዝ መኪና አይታይም፣አልፎ አልፎ ዋዝና አይፋ የመከላከያ ሠራዊት መኪናዎች ተከታትለው ያልፋሉ። ቁልቁለቱን እየወረድን በስተቀኝ ሰፊ የተቃጠለ ቁጥቋጦ አይቼ ምን እንዳቃጠለው ጠየቅሁ። እንደተነገረኝ ከዚህ ኮረብታማ ስፍራ ላይ የሻቢያ ጦር አድፍጦ በመመሸግ በዋናው መንገድ ወደ ምፅዋ የሚጓዝውን ብዛት ያላቸው ቀለብና መሣሪያ የጫኑ (convoy) መሃል ላይ ቆርጦ ተኩስ በመክፈት እንዳጋዩትና፣ከዚህም የመሣሪያና የነዳጅ ቃጠሎ የተነሣ በአካባቢው ያለው ቁጥቋጦ እንደተቀጣጠለ ነገሩኝ። እጅግ የሚያሳዝን ሥፍራ!

ወደ ምፅዋ መግቢያ ላይ የመከላከያ ሠራዊት ካምፕ ከቅርብ ርቀት ይታያል። አለፍ-አለፍ ብሎ መንገዱ በታጠቁ ወታደሮች ተወጥሯል። ምፅዋን በፊት የማውቃት ሆና አላገኘኋትም፣ ቤቶቹ በሙሉ በጥይት ተበሳስተውና ፈራርሰው አቧራ ለብሰዋል፣ በርና መስኮቶቹ ጭምር ቀለማቸው አኮፍኩፎና አርጅቶ ወይበዋል። በመንገዱ የሚዟዟር ሰው አይታይምና የሰው ያለህ ያስብላል! ባጭሩ የተወረረ ከተማ ይመስል ነበር። ወደምናርፍበት ቀይ ባህር ሆቴል (Red Sea Hotel) አመራን። ብቸኛው ባለ ሦስት ኮከብ ሆቴል ሲሆን ክፍሎቹ ንፁህ ናቸው፣የግቢውም ዛፍ አድጎ ነፋሻማ አየር ያመጣል። ባይገርማችሁ በሆቴሉ የነበርነው እንግዶች ከአምስት አንበልጥም፣አልፎ አልፎ የወደብ ኃላፊዎች በምሳ ሰዓት መጥተው ይስተናገዳሉ። የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ከአ/አበባ በዝውውር የተመደበ የመሃል አገር ሰው ነበር፤(ፀጋዬ ይሁን ተስፋዬ ስሙን ዘነጋሁት)። በሆቴሉ በቂ እንግዳ አለመኖሩና የሚያናግረውም ሰው ባለመኖሩ፣ብቸኛም በመሆኑ በጣም እንደሚደበር (depressed

እንደሚሆን) እና ከዕለት ወደ ዕለት ስጋት እንደሚገባው አወጋኝ።

አንድ ቀን ሆቴል ምሳ ላይ እንዳለን ከወትሮው የተለየ ግርግር በዛና እንደ ቆቅ አንገታችንን አቅንተን በድንጋጤ ስንመለከት በርከት ያሉ የመከላከያ መኮንኖች ሲገቡ አየን፤ለካስ የመከላከያ ሚኒስቴሩ ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ከፍተኛ መኮንኖችን አስከትለው ለጉብኝት መጥተው ኖሯል። ከእርሳቸውም ጋር (የቀድሞው) ኤርትራ ክ/ሀገር የጦሩ የበላይ ዋና አዛዥ ሜ/ጄኔራል ደምሴ ቡልቱ እና ሌሎችም ከፍተኛ መኮንኖች ነበሩ፣ ከመካከላቸው በቅርብ የማውቃቸው ሰዎች አየሁ፤አንደኛው ብ/ጄኔራል ታደሰ ፈረደ (ከኮሜርስ በ1960 ዓ/ም የተመረቀ) እና ሌላው እውቁ ጋዜጠኛ ጌታቸው ኃ/ማርያም ነበሩ። (የሁለቱንም ነፍስ እግዜር ይማር)

ጌታቸው ኃ/ማርያም ከማስታወቂያ ሚ/ር በዝውውር አስመራ የተመደበና ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ሲመጡ አብሮ ዜና እንዲዘግብ የተመደበ ነበር። እንደተረዳሁት ሁሉም ሳያድሩ እለቱን ወደመጡበት አስመራ ተመልሰዋል።

ወደ መጣሁበት ጉዳይ ልመለስና ከኢጣሊያ መንግሥት የተላከው የእርዳታ ብስኩት በአንድነት (ANDINET) መርከብ በተባለው ቀን ምፅዋ ወደብ ገብቶ አገኘነው። የቆንስላው ተወካይ፣የጉምሩክ ተወካዮችና እኔ በመሆን፣ አንድ በአንድ ኮንቴይነሩ እንዲከፈት አደረግን። ቆጠራ ከተካሄደ በኋላ አስፈላጊ ልዩ ልዩ ፍተሻዎችን አድርገን እንዳበቃን፣ ለተጨማሪ (Quality) የላብራቶር ምርመራ ከእያንዳንዱ ኮንቴይነር አንድ-አንድ ካርቶን ብስኩት ለናሙና ወሰድኩ። የኮንቴይነር ተርሚናል/ማሳረፊያ ቦታ ከወደብ ውጭ ባለ ስፍራ ሲሆን፣ ፍተሻ በምናከናውንበት ወቅት የአካባቢው ትናንሽ ወጣት ልጆች (ምናልባትም የተከፈተው ብስኩት ሽቷቸው ይሆናል) ከበውን ነበር። የልጆቹን ሁኔታ በአዘኔታ ተመልክቼ ከወሰድኩት ናሙና የተወሰነውን ለልጆቹ ለማከፋፈል ወሰንኩ። አብረውኝ ለነበሩትም «ዞሮ ዞሮ የተላከው ብስኩት ለነዚህ መሰሎቹ ነው በማለት» አሳምኜ አሳቤን ደገፉት። በዚህ አጋጣሚ የተገነዘብኩት ግን፣ ብስኩትን ለመቀበል የሚሻሙት ልጆች በብዛት ሴቶች መሆናቸውን ነበር። በመገረም «የምፅዋ እናቶች የሚወልዱት ሴት ብቻ ነው እንዴ?» ብዬ አንዱን የጥበቃ ጓድ ስጠይቀው የመለሰልኝ፣ «ወንዶች ልጆችማ ገና ከፍ ሲሉ ተመልምለው ጫካ ይገባሉ» በማለት ነበር።

Signor Di Mascio ተጨማሪ ቀናት ምፅዋ እንደሚቆይ ነገረኝና፤እኔ ሥራዬን ያጠናቀቅሁ በመሆኑ በማግሥቱ ወደ አስመራ ለመመለስ ወሰንኩ፣ ስለዚህ ተመላሽ ሰዎች አግኝቼ ከእነርሱ ጋር መንገድ ጀመርን። ግማሽ መንገድ እንደሄድን አንድ ምስኪን ወታደር ሊፍት ጠየቀንና አሳፈርነው። ይህ ሰው ከክሳቱ ብዛት ዓይኑ ወደ ውስጥ ጎድጉዶ የፊት አጥንቱ ወጥቶ ይታያል፣ የፀሐይ ሐሩርም ከሰል አስመስሎታል፤በዚህ ጠራራ ፀሐይ የለበሰው ጥቁር አረንጓዴ ካኪ የሚሊሻ ዩኒፎርም ሲሆን፣ ክላሽ ጠመንጃም ተሸክሟል። ሲናገር ትንፋሹ ቁርጥ-ቁርጥ ይላል፤ድምፁ ከመሰለሉ የተነሳ ብዙም አይሰማም ነበር። ሚሊሻ ወታደር መሆኑን ነግሮን፣ «ምን ልትሠራ ከካምፕህ ወጣህ? ብዬ ጠየኩት፣እርሱም መልሶ «የዕለት-ተዕለት ምግቡ / ኮሾሮ» ሰልችቶት እንጀራ በወጥ አምሮት ሊመገብ መውጣቱን ነገረን። «አይ የዋህ ምስኪን! አሉ አብረውኝ የነበሩት፣ «የእሳት እራት» እንዳይሆን በመስጋት! መቼም ደፍሮ የወጣው የተለመደና የማያሰጋ ቢሆን ነው! አልኳቸው። ቀጥዬም «ለመሆኑ ትውልድህ ከየት አካባቢ ነው፣ያለህበት ቦታ ከመጣህስ ስንት ዓመት ሆነህ» አልኩት። በእውነት ያሳዘነኝና ያስገረመኝ መልስ «ከየት እንደመጣሁ ረስቼዋለሁ» ሲለኝ ነው። እንዴት?ምን ነበርክ -ገበሬ ወይስ ተማሪ ?ስለው «ከወጣሁ እኮ ቆይቻለሁ ብዙ ዓመት ነው፣ ሲመስለኝ ግን ገበሬ ነበርኩ፣ብዙም ትምህርት የለኝም» አለኝ። ብዙ የሚያሳዝኑ ክስተቶችን አወጋን፣ እንዲያው ተከድኖ ይብሰል ማለቱ ሳይሻል ይቀራል! ወደ አፋፉ ከፍ እንዳልን የሚፈልገው ስፍራ መድረሱን አመለከተንና አውርደነው መንገዳችንን ቀጠልን፣አስመራም በጊዜ ደህና ገባን። እኔም አንድ ቀን ብቻ አድሬ በማግስቱ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

አስቀድሜ እንደገለጽኩት ብዙ ሥራዬ ወደ አሰብ የሚያመላልስ ነበር፤ለመጨረሻ ጊዜ አሰብ የበረርኩት በሰኔ ወር 1983 ዓ/ም ነበር። ኤየር ሰርቭ (Air Serve) የሚል በአለም ምግብ ድርጅት /ትራንስፖርት ዩኒት(UN W.F.P) ንብረት የሆነ አነስተኛ አውሮፕላን በመብረር ነበር። በዚያን የመጨረሻ ወቅት አንድ መርከብ አሰብ ወደብ ላይ የእርዳታ ስንዴ በማራገፍ ላይ እንዳለ ከተማው በተኩስ ይናወጥና ተፋላሚው ጦር እየገፋ መምጣቱን የተገነዘበው የመርከቡ ካፒቴን ለአደጋ ከመጋለጡ በፊት፣ስንዴ ማራገፉን አቋርጦና ያልተራገፈውን ከፊል ቋት (hatch) ስንዴ እንደያዘ ወደ ጅቡቲ ይነጉዳል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምን ያህሉ ስንዴ አሰብ ወደብ እንደተራገፈና ምን ያህሉ ጅቡቲ ላይ እንደተራገፈ ለማጣራት ከተላኩት አንዱ ነበርኩ፤(ይህም የሆነው የኤስ.ጂ.ኤስ ተወካይ

በመሆኔ ነው)። የቡድኑ መሪ ማይክል ኤሊስ የተባለ (Micheal Ellis/UN W.F.P.Director) ሲሆኑ፣ከአውሮፖ ሕብረት (EU) ሁለት ተወካዩች፣ ለአሰብ ወደብ የ W.F.P ተጠሪ/ኃላፊ ሆኖ የተሰየመ አንድ የዴንማርክ ዜጋ እና የ S.G.S Food Aid Monitoring Service Managing Director,Marc Grandjean ነበርን።

የአንድ ሰዓት ከሃያ በረራ በነበረው ጊዜ የደራው ወሬ ስለ ኤርትራ ነፃነት ጉዳይ ሲሆን፣ከብዙ የአድናቆት ወሬ መካከል የሚገርመው አንደኛው የተናገረው “አስመራ ስለተመገበው ግሩም የሆነ የቦሎቄ ሾርባና የጥጃ ሥጋ አሮስቶ” ነበር። ከማርክ ግራንዣ በቀር ሌሎቹ አድናቂና አድማቂ ነበሩ። ከአሸናፊው ጋር መወገን የተለመደ ባህል ነውና! አሰብ እንደ ደረስን፤ የ W.F.P መኪናና ሹፌር ተመድቦልኝ እኔ ወደ ማሪታይም አሰብ ቢሮ አመራሁ፤ቀድሞ የMartime & Transit Service Corp. ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የነበረው ቀርቶ፣በአዲስ ስያሜ Eritrean Shipping & Transit Agency Services በሚል ተተክቷል። የነበሩት ሠራተኞች በሙሉ ስለሚያውቁኝ ሳይታሰብ በመምጣቴ ተደናግጠው ነበር የተቀበሉኝ። ሁሉም የአገሩ ተወላጆች ቢሆኑም፣ ሹመቱ ተገለባብጦ፣ የበታች የነበረው በአዲስ ምደባ የበላይ ሆኖ ተሹሟል፤ የበላይ የነበረው ደግሞ አንገቱን የደፋ ተራ ሠራተኛ ሆኖ አገኘሁት። ስለዚህ አዲሱ ኃላፊ ጋር በመሄድ የመጣሁበትን ጉዳይ አስረድቼ የምፈልጋቸውን መረጃዎች አገላብጬና ከወደብ ሪከርድ ጋር አመሳክሬ፣ መረጃውን ይዤ፣ ወዳጆቼን በየቢሯቸው ሄጄ ተሰናበትኩ። በወቅቱ አ/አበባ ላይ የሰዓት እላፊ ገደቡ ከምሽቱ 1:00 ሰዓት በመሆኑ ቀድሜ አሰብ ኤየር ፖርት ደረስኩ፤ አሰብ የተመደበው የ W.F.P ተወካይ ሲቀር ሌሎቹ አራቱ መጡ። ከማርክ ግራንዣ በስተቀር ሁሉም ፊታቸው ቲማቲም መስሎ አኩርፈው አይነጋገሩም ነበር። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ቀስ ብዬ ማርክን ጠየኩት። <I’ll tell you later> አለኝ፣ፊታቸው ላለመናገር ፈልጎ።

አውሮፕላን እንደገባን፣ማርክ ሳይነግረኝ በፊት አንዱ ንዴት በተቀላቀለ ስሜት <These bushmen think bush way> አለ። ከዚያም የሆነውን ነገር ማርክ እንዳጫወተኝ፣ የወደቡ ተወካይ/ኃላፊ አስቀድሞ የተነገረው በመሆኑ ቢሮው ሆኖ መጠባበቅ ሲገባው ስላልነበረ፣ አንድ ሰዓት ያህል ጠብቀው አ/አ መመለሻችን ሳይረፍድ ወደብ ገብተው ይጎበኙ ጀመር። በኂላ ላይ ዘግይቶ ኃላፊው ሲመለስ ወደቡ ውስጥ ሲዘዋወሩ ያገኛቸውና (who are you?) ብሎ ከፍ ዝቅ አድርጎ አዋርዶ get out! ይላቸዋል። የመጡበትንም ጉዳይ በጥሞና ሊያስረዱት ቢሞክሩም መጀመሪያ የወደቡን ሕግ ጥሳችኂል፣«ዞር በሉ!» ይላቸዋል። በሁኔታው ተናደው ምንም ሳይመልሱ ይወጣሉ።

ቀድሞ ስንመጣ የነበረውን አድናቆትና ማሞካሸት ባንድ ጊዜ ገደል ከተውት፣ ስንመለስ በስድብና በእርግማን ለወጡት። በሰዓታት ውስጥ ከመጠን በላይ ያደነቋቸውን ሰዎች አንስተው ገደል ጨመሯቸው! ኃላፊውን ወዲ... አደነቅሁት፣ ለሁሉም ጊዜ አለው ይባል የለ! አንጀቴም ቅቤ ጠጣ ! በሰላምም አዲስ አበባ ገባን።

ቀጥዬ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ አስመራ የሄድኩት በነሐሴ ወር 1983 ዓ/ም ነበር፣የያኔው ጉዞዬ፣ አሰብና ምፅዋ ወደብ ላይ የነበረኝን የቀድሞ ሥራ (ከኤርትራ ተወላጆች ጋር በመሻረክ) ለመቀጠል የሚያስችል የሥራ/የንግድ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ለመጠየቅና እግረ መንገዴንም የተንጠለጠሉ/ያልተዘጉ ሥራዎች ስለበሩኝ ለማጠናቀቅ ነበር። ከአ/አበባ ስንነሳ ከአቶ ለዓከማርያም ኦቅበ-ሚካኤል (የኢትዮ አውቶሞቲቭ ንግድ ድርጅት) ሥራ አስኪያጅ ጋር አብረን ተሳፍረን ስለነበር፤ አውሮፕላን ውስጥ እያወራን ነበር። አስመራ መዳረሻ ላይ አውሮፕላኑ ዝቅ እያለ ልክ መሬቱን ሲረግጥ የተደበላለቀ እልልታና ፈንጠዚያ ሆነ። ከደቂቃዎች በኂላ በተለያየ ስሜት ውስጥ ያለነው ሁሉ ተረጋግተን መውረድ ጀመርን። ሻንጣችንን ከመረከባችን በፊት የመግቢያ ፈቃድ እያሳየን ወደ ውስጥ ስንዘልቅ፣ወንበር ይዘው የተቀመጡ ሰዎች ከመንገደኞች በፈቃደኝነት እርዳታ ይሰበስቡ ነበር። እኔም የምን እርዳታ ነው ብዬ ጠይቄ «ለኤርትራ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ማቋቋሚያ» ብለውኝ ብር 50.00 ለግሼ ደረሰኝ ተቀብያለሁ። (እንዲያውም ይህን ደረሰኝ አ/አ ለነበሩትና ክለባችንን ለሚያዘወትሩት ወዳጆቻችን ገ/መስቀል ተአረና አብርሃ ዮሐንስ /ሼል/ አሳይቻቸው ነበር።

አስመራ ያረፍኩት የጥንቱ እምባሶራ ሆቴል ነበር፤ሆቴሉ ውስጥ ጥቂት የውጭ ዜጐችና አ/አ ነዋሪ የሆኑ ልጆቻቸውን ለማስጐብኘት ይዘው የመጡ ከበርቴዎች ነበሩ። ማታ ላይ አቶ ለዓከ መኪና ይዘው ሆቴል መጡና አንድ የመዝናኛ ቤት ወሰዱኝ፤ ቤቱ ሙሉ ነበር። አቶ ለዓከ በአስመራም የተከበሩ ሰው ነበሩና ሙሉ ጠርሙስ ብላክ ሌብል አወረዱ፣ እኔ ብዙም መጠጥ ስለማልደፍር በመለኪያ ይታዘዝ ብልም፣ ግድ የለህም እንደሰት ብለው ጠርሙሱ ተከፈተ። አንድ ሁለት እያልን መጠጡን ተያያዝነው፤ ሙዚቃውም ይጮሀል፣ እኛም ለመደማመጥ እንጮሃለን። የሚገርመው

የአማርኛም የትግርኛም ዘፈኖችን እኩል ለእኩል ይዘፈኑ ነበር።

ታዲያ እዚሁ ጠባብ ቤት አዳዲስ ሰዎች ይገቡ ጀመርና አማትሬ ስመለከት አንድ አ/አ የማውቀው ሰው አየሁ። ዘርዑ ወ/ሚካኤል ይባላል፤ የኢት.ኢንሹራንስ ኮ/ን የምዕራብ ቅ/ፍ ሥራ አስኪያጅ ነበርና ለከፍተኛ ትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር ተልኮ ኮርሱን ሲጨርስ ወደ አገር ቤት አልተመለሰም። በዚያው በረሃ ገብቶ ኖሮ ከበረሃ መልስ በነበረው ሙያ የኤርትራ ብሔራዊ ኢንሹራንስ ኩባንያን እንዲመራ ተሹሞ ነበር። ከዘርዑ ጋር ሞቅ ያለ የወዳጅነት ሰላምታ ተለዋውጠን ቁጭ ብለን ማውራት ጀመርን። የመጣሁበትን ጉዳይ አስቀድሞ ሲጠይቀኝ ደስ አለኝ፤ በኔ ግምት ስለምንተዋወቅ እንደሚረዳኝ ተማምኜ ነበርና የመጣሁበትን ጉዳይ ባጭሩ ገልጬ፤በሽርክናም በኩል ከአገሩ ተወላጅ ሽሪክ (partner) ጋር ለመጣመር ፍላጎት እንዳለኝ ነገርኩት። ምን የመለሰልኝ መሰላችሁ፤ «እንኳን ላንተ ለመሃል አገር ሰው ይቅርና፣አ/አበባ ተቀምጠው መኪያቶ ሲጨልጡ ለኖሩትም ኤርትራውያን የንግድ ፈቃድ አይሰጥም፤የንግድ ፈቃድ የሚሰጠው የመከራውን ዘመን እዚሁ አካባቢ ለኖሩ ብቻ ነው» አለኝ። ሌላም መመዘኛ ሊኖር ይችላል፣ እኔ ግን እንደማይሰጠኝ ተረዳሁና ተሰነባበትን። እዚያው ቤት እንዳለሁ ኃ/ማርያም እስጢፋኖስ ከኮሜርስ በ1959 ዓ/ም የተመረቀና የቅርብ ጋደኛዬ የነበረን አገኘሁት። ከርሱም ጋር የሞቀ ሰላምታን ተለዋውጠን የመጣሁበትን ጉዳይ ነገርኩት፤ ምስኪን ለፍቶ አዳሪ ኦዲተር ነበርና፣ ብዙም ስለ አዲሱ አስተዳደር የሚያውቀው ነገር እንደሌለ አጫወተኝ። የሚያወራውም በጥንቃቄና ፍራቻ በተሞላበት ነበር።

በሌላ ቀን ዞር ዞር ብዬ ከተማውን ጎበኘሁት፤ቀን ላይ ብዙ ሰው ሲዘዋወር አይታይም ነበር፣ ምሽት ላይ ምግብ ቤቶች/ሬስቶራንቶች ባዷቸውን የተመጋቢ ያለህ ብለው ደርቀው ይታዩ ነበር፣ የሆቴል ባለቤቶች በር ላይ ቆመው «በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ አሮስቶ፣ ላዛኛ፣ወዘተ፣አለ» በማለት መንገደኛ እንዲገባና እንዲስተናገድ ሲጋበዙ ታዝቤአለሁ። ብዙ የውጭ ተስተናጋጅ ሰው/ቱሪስት አልነበረም፤ሌላ የተወረረ ከተማ ሆኖ አገኘሁት። ካረፍኩበትም ሆቴል በእራት ሰዓት የማያቸውም እንግዶች በጣም ውሱን ነበሩ። የኔም ጉብኝት አብቅቶ ተመለስኩ፤ ለካ ጊዜው ሮጧል፤24 ዓመት አልፎታል፤ምናልባት አሁን ተቀይሮ ይሆን? አንድ ቀን ግን «ናይ ቀደም ፍቅሪ አሥመሪና» ተመልሼ የማያት ይመስለኛል። ቸር ይግጠመን!